# የእውነታ ሉህ ቁ. ፲
# የዘር ልዩነት ድህነት በምግብ እና በውኃ ዋስትና ላይ ያለው ተጽዕኖ

## በዘር የተለዩ ሰዎች በምግብ እና በውሃ ዋስትና እንዴት ነው የተጎዱት?



ኦንታሪዮ በካናዳ ውስጥ በጣም የባሰች ነች! እ.ኤ.አ. እስከ 2011 ድረስ፣ በካናዳ ውስይ ከፍተኛው የምግብ እጥረት የነበረው በቶሮንቶ (10.1%) እና በሰሜን ኦንታሪዮ (9.7%) እንደሆነ ሪፖርት ተደርጓል።

**ማኅበራዊ ድጎማ**: እ.ኤ.አ. ከ2011 ዓ.ም. ጀምሮ በኦንታሪዮ ውስጥ 70% የሚሆኑት ቤተሰቦች የገቢ ምንጫቸው ማህበራዊ ድጎማ ሲሆን የምግብ ዋስትናም የሌላቸው ነበሩ።
**ገቢ፡** በኦታዋ በኩል ከተቆረጠው ዝቅተኛ ገቢ በታች ከሚኖሩት ቤተሰቦች 20.2% የሚሆኑት ከመጠነኛ እስከ ከባድ የምግብ ዋስትና ችግር ላይ እንደ ወደቁ ሪፖርት አድርገዋል። ይህም ከኤል አይ ሲ ኦ (LICO - የገንዘብ ችግርን ለመለካት የሚደረግ ዝቅተኛ የገቢ ቅነሳ ልኬት) በላይ ከሆኑት 3.5% ጋር ተነጻጽሮር ነው።
**ትምሕርት ቤት፡** በቤት ውስጥ የምግብ ዋስትና አለመኖር ከ18 ዓመት በታች ከሆኑት ከስድስት የካናዳ ሕፃናት ውስጥ አንዱ ላይ ችግር ያስከትላል። ካናዳም ከአሜሪካ እና ከሌሎች በኢንዱስትሪ ከበለጸጉት አገራት በተለየ መልኩ ብሔራዊ የትምህርት ቤት ምግብ ፕሮግራም የላትም።

**የቅርብ ጊዜ ኢሚግሬሽን፡** እ.ኤ.አ. በ2012 –2012፣ 1.1 ሚሊዮን የሚሆኑ የካናዳ ቤተሰቦች የምግብ ዋስትና ችግር አጋጥሟቸዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከመጡት ሰፋሪዎች (19.6%) መካከል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመጡ ካልሆኑት ስደተኞች (11.8%) እና ከካናዳ ከተወለዱት ብዛት (12.4%) ጋር ሲነፃፀር በዋነኛነት ባለቀለም በሆኑት ሰዎች ላይ ከፍ ያለ ነበር፣

**ማህበራዊ / መዋቅራዊ ውሳኔ ሰጪዎች፡**
በቶሮንቶ የሚገኙት የላቲን አሜሪካውያን ስደተኞችን የምግብ ዋስትና አለመኖር ምክንያት ሦስት ተዛማጅ ዋና ዋና መመዘኛዎች ተገኝተዋል፣ እነዚህም - ማህበራዊ ድጎማን እንደ ዋና ገቢ፣ የምግብ ባንኮችን መጠቀም፣ እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ውሱንነት።

**የባህል መጣጣም፡** የአገሬው ተወላጆች እና የቀለም ሰዎች በተለምዶ የሚስማሙ ባህላዊ ምግቦችን እና ተገቢነት ያላቸውን ምግቦች በሕዝባዊ ተቋማት እና በምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች ውስጥ ማግኘት እንደማይችሉ ያምናሉ። ምክንያቱም እነዚህ እንደ አስፈላጊ ሳይሆን እንደ ቅንጦት ይታያሉና።

**አዲስ መጤ ሰፋሪዎች፡** በካናዳ ውስጥ ያሉ ስደተኞች በምግብ ዋስትና እጥረት ምክንያት የመቸገር ዕድላቸው በእጥፍ ከፍ ያለ ሲሆን፣ እዚህ ከደረሱ በኋላም የጤንነት ማሽቆልቆል አዝማሚያ ይታይባቸዋል።

## ነባር የአገሬው ተወላጅ ትኩረት

እ.ኤ.አ. ከ2004 እስከ 2014 ባለው ጊዜ መካከል በካናዳ ውስጥ ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት ቀደምት ሕዝቦች (First Nations) ቢያንስ በአንድ የውሃ አማካሪ (ውሃው እንደተበከለ የሚጥቁም የህዝብ ማስታወቂያ) ሥር ኖረዋል።

**43**

በኦንታሪዮ ውስጥ 46 የሚሆኑ የረጅም ጊዜ የመጠጥ ውሃ አማካሪዎች እስከ 2018 ድረስ በ25 የአገሬው ተወላጅ ማህበረሰቦች ውስጥ ነበሩ።

90% ከመቶ የሚሆኑ የግራሲ ናሮውስ እና ዋባሲሙን ኗሪ ቀደምት ሕዝቦች ከውቢጎን-የእንግሊዝ ወንዝ ሲስተም ለሚመጣው ሜርኩሪ መጋለጥ ምልክቶች አሳይቷል።
የአገሬው ተወላጅ ቤተሰቦች ከፍተኛ የምግብ እጥረት የማጋጠም ዕድላቸው ከፍተኛ ነው።
5.1% በመቶ የሚሆኑ የአገሬው ተወላጅ ቤተሰቦች አነስተኛ የምግብ ዋስትና ችግር፣ 14.8% በመቶ የሚሆኑ መካከለኛ የምግብ ዋስትና፣ እንዲሁም እና 8.3% በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ከባድ የምግብ ዋስትና ችግር ያጋጥማቸዋል።
በቶሮንቶ ውስጥ 20% የሚሆኑት የአገሬው ተወላጅ አዋቂዎች በሚኖሩበት ቤተሰብ ውስጥ ቢያንስ የሚበላው በቂ ምግብ ከሌለው ከአንድ ሕፃን ልጅ ጋር እንደሚኖሩ አመላክተዋል።

እ.ኤ.አ. በ2011 ዕድሜያቸው 18 እና ከዛ በላይ የሆኑ የአገሬው ተወላጅ ሰዎች በግምት 29% በመቶ የሚሆኑት በቂ ምግብ በሌላቸው ቤተሰቦች ውስጥ እንደኖሩ ታውቋል።
የባህላዊ እና የፍጆታ ምግቦች ተደራሽነት የምግብ እጥረትን ለመቀነስ እና በአገሬው ተወላጆች መካከል ጤናን ለማሻሻል አስፈላጊ ዘዴዎች ናቸው።
74% በመቶ የሚሆኑ በቶሮንቶ ውስጥ ከሚኖሩት የአገሬው ተወላጅ ሰዎች ዛሬ ከሚመገቡት የበለጠ ባህላዊ ወይም የሀገር ምግብ መመገብን ይመርጣሉ።

**ከመካከለኛ እስከ ከባድ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸው በካናዳ ያሉ ቤተሰቦች በመቶኛ አሃዝ (2007- 2010), እ.ኤ.አ. በ2013 እና በ2015 ሪፖርቶች መሠረት፤**






* ሌሎች ጥናቶች እንደሚጠቁሙት በኢንዩት ቤተሰቦች ውስጥ የምግብ ዋስትና አለመኖር ከፍተኛ ሆኖ ከ62% በላይ ሊሆን ይችላል ይላሉ።

**የምግብ ዋስትና** ማለት በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ አቅማቸው የፈቀደውን ምግብ ያገኛሉ ማለት ነው፤ ይህም፡ ጤናማ እና ደህና፣ ለቤተሰቦቻቸው በቂ፣ ከአካባቢያዊ መደብሮች የሚገኝ (ከምግብ ባንኮች እና ከመጠለያዎች ይልቅ)፤ ለአካባቢ በሚስማሙ መንገዶች የበቀለ፣ ባህላዊ አግባብን የጠበቀ፣ የታወቀ እና ተስማሚ!

የውሃ ዋስትና ማለት በቂ የምግብ እና የሸቀጣሸቀጦች ምርት መስፈርቶችን ለመጠበቅ፣ ተገቢ ንጽህና ያለው፣ እንዲሁም ዘላቂ
ጤናን እና ደህንነትን ለመጠበቅ የሚረዳ በቂና ንፁህ የሆነ የመጠጥ
ውሃ አቅርቦት ያለ የተደራሽነት አቅም ተብሎ ሊገለፅ ይችላል።

Aa

## ፈጣን ማስታወሻዎች

ስለ ባለ ቀለም ህዝቦች ስንነጋገር የዘር መሠረታችውና ቅሬተ-ቅርሳቸው ከአውሮፓ ያልሆኑትን ካናዳውያንን ማለታችን ነው። እነዚህም ካናዳ ውስጥ የተወለዱና ከካናዳ ውጭ የትም የተወለዱ፣ በሁለቱም ጎራ ስላሉ የቀለም ሰዎች መናገራችን ነው።
ነባር የአገሬው ተወላጆች ስንል በአገሪቱ የነበሩ ቀደምት ህዝቦች {First Nations / Natives} [የተመዘገቡና እውቅና የተሰጣቸው እንዲሁም ያልተመዘገቡ) ሜቲስ እና ኢንዩት ስለሚባሉ ሕዝቦች ነው።
በቶሮንቶ ውስጥ በድህነት ከሚኖሩት ሰዎች ውስጥ 62% የሚሆኑቱ በዘር ልዩነት ከሚታዩ ቡድኖች የመጡ ናቸው፡በካናዳም በዘር ልዩነት ከሚታዩት ውስጥ 52% የሚኖሩት በኦንታሪዮ ውስጥ ነው።

በካናዳ ውስጥ በዝቅተኛ ገቢ ተቆራጭ (LICO) ወይም በዝቅተኛ የገቢ ልኬት (LIM) የሚመደቡ ቤተሰቦች ከገቢዎቻቸው ውስጥ በጣም ከመቶኛ ውስጥ ትልቁን የሚያጠፉት በአስፈላጊና መሠረታዊ ነገሮች ማለትም እንደ ምግብ እና መጠለያ የመሳሰሉት ናቸው። ድህነትን የምንለካውም በዚህ መንገድ ነው።

**ስልታዊ ዘረኝነት** ብዙዉን በስውር በሚሠራ ተቋማዊና የተዛባ ፖሊሲ፣ ልምምድና አሠራር ምክንያት የሚፈጸም ሆኖ በተለያዩ ቡድኖች መካከል አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ አሠራር ነው።
የተወሰኑ ቡድኖችን በተለያዩ መንገዶች እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል አስቀድሞ ግምት ውስጥ ያላስገባ፣ ሁልጊዜም እንደተለመደው አካሄድ ብቻ የመከተል ውጤት ሊሆን ይችላል።

# ምን እየተደረገ ነው?

**አፍሪ-ቃዊ የምግብ ቅርጫት** [afri-can food basket] ማለት በማኅበረሰቡ ላይ የተመሠረተ፣ ለትርፍ ያልሆነ የትብብር ህብረት ልማት እንቅስቃሴ ሲሆን ይህም የአፍሪቃውያን ካናዳውያንን ማህበረሰብ አባላት የምግብ፣ የጤና እና የሥራ መቀጠር ፍላጎቶችን ለማሟላት፣ በተለይም በኢኮኖሚያዊ እና በማህበራዊ ጉዳዮች ተጋላጭ ለሆኑ ቄርጦ የተነሣ ድርጅት ነው።
www.africanfoodbasket.com / info@africanfoodbasket.ca

**አክሰስ አልሊያንስ** የአዲስ መጤዎችን የምግብ ባንኮች ተደራሽነትን ለማሳደግ እና ባህላዊ አግባብነት ያላቸውን የአገልግሎት አሰጣጥ ሞዴሎችን ለማዳበር ከምግብ ባንኮች እና ከደጋፊዎች ጋር አብሮ የሚሠራ ነው።
www.accessalliance.ca / communications@accessalliance.ca

**ፉድ ሼር** የምግብ ዋስትናን ለማሳደግ ብዙ የፖሊሲ ለውጦች እና እርምጃዎችን መውሰድ፣ እንደ መሠረታዊ ዝቅተኛ የገቢ ደረጃዎች፣ መመዘኛዎችን እና በሥራ ውስጥ እኩልነትን የሚያሳድጉ ፖሊሲዎች የመሳሰሉትን ለመቅረጽ ምግብን እንደ መሠረታዊ የሰብዓዊ መብት ጉዳይ አድርጎ ይሠራል።
www.foodshare.net / info@foodshare.net